በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

??/? /?? ? 214389
?? 22/9/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - አቶ ገዛሄኝ ጉታ ፡ የቀረበ የለም

ተጠሪ - አቶ ማርቆስ ባልቻ ፡ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መስከረም 15 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 376464 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 343284 ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34778 መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 65240 የካቲት 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የውርስ ንብረት በፍ/ቤት በውርስ አጣር ሳይጣራ እና ክፍፍል ሳናደርግበት ተከፋፍላችኋል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከደንዲ ወረደ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ጣልቃ ገብ ደግም አሁን ክርክር ውስጥ የሌለው አቶ አበራ ጉታ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ከሳሽ ባቀረበው ክስ እናቴ ወ/ሮ ጡሬ ሚጀና በ1986 ዓ/ም ሞታለች፡፡ እኔና ተከሳሽ በእናት ወንድም ስንሆን የእናታችን ንብረት በደንዲ ወረዳ ጊንጪ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያለው የመኖሪያ ቤት በ288 ካ/ሜ ላይ ያረፈ 3 ቤቶች እስከ 2004 ዓ/ም በእናታችን ስም ስንገብርበት የነበረና ከ2004 ዓ/ም በኋላ በሶስታችን ስም አበራ ጉታ ጨምሮ ስንገብርበት ቆይተናል፡፡ ይሁንና ተከሳሽ ሳናውቅ በስሙ ያስመዘገበ በመሆኑ ድርሻችንን ያካፍለን ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሽም የአሁን ተጠሪ ክስ ያቀረበበት የመሬት ይዞታ 200 ካ/ሜ ብቻ ነው፡፡ እናታችን በ1986 ዓ/ም የሞተች ሲሆን፣ እናታችን በህይወት እያለች በ288 ካ/ሜ ቦታ ላይ የተሰራ ቤት ነበራት፡፡ ያ ቤት አሁን የለም፡፡ የእናታችን የመሬት ይዞታ የድሮ ይዞታ ስለሆነ 500 ካ/ሜ የነበረና እናታችን ከሞተች በኋላ በስማችን አስመዝግበን ተከፋፍለን በ200 ካ/ሜ ላይ ካርታ ተሰጥቶኛል፡፡ በዚሁ መሰረተ የእናታችን አሮጌ ቤት አፍርሼ ሰርቻለሁ፡፡ አቶ አበራ ጉታም 150 ካ/ሜ ደርሶት ቤት ሰርቶበት ይገኛል፡፡ ይህ ሆኖ እያለና ድርሻውን ወስዶ እያለ የኔን ድርሻ እንዳካፍለው መጠየቁ ተገቢ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ጣልቃ ገብ አሁን በክርክር ውስጥ የሌለው አቶ አበራ ጉታ በጣልቃ ገብነት ባቀረበው ክርክር እናታችን ጥላ የሞተችው የመሬት ይዞታ 500 ካ/ሜ ነው፡፡ ከተማ አስተዳደሩ የድሮ ይዞታ ስመዘግብ ስትገብርበት የነበረው በ288 ካ/ሜ ቢሆንም ይዞታው 500 ካ/ሜ በመሆኑ በ500 ካ/ሜ ገብረንበት የነበረና ተከፋፍለን እኔና ከሳሽ 150 ካ/ሜ ተከሳሽ ደግሞ 200 ካ/ሜ ደርሶን የእናታችን ቤት ተከሳሽ በደረሰው ድርሻ ላይ ያረፈና አርጅቶ በመፍረሱ ተከሳሽ ሌላ ቤት ሰርቶበት እኛም በደረሰን ቦታ ላይ ቤት ሰርተንበት አስመዝግበን ይዘን የምንገኝ ሲሆን ይህ ሆኖ እያለ ከሳሽ ክስ ማቅርቡ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ ይሁንልን ብሏል፡፡ የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 65240 የካቲት 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የተሰሙት ምስክሮችና የቀረበው የሰነድ ማስረጃ እናታቸው ጥላ የሞተችው ይዞታ 500 ካ/ሜ ሲሆን ስትገብርበት የነበረው በ288 ካ/ሜ የነበረና ከተማ አስተዳደሩ ሲለካ 500 ካ/ሜ በመሆኑ በ500 ካ/ሜ መዝግቦላቸው ተከፋፍለው ይዘው እንደሚገኙና ተከሳሽ የእናታቸው ቤት ደርሶት ቤቱን አሳድሶ ኩሽናና ሽንት ቤት ሰርቶበት በስሙ አስመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ በመረጋገጡ ወራሾች ተስማምተው ተከፋፍለው ይዘው የሚገኙትን የተከሳሽ ድርሻ ላይ ከሳሽ ክስ ማቅረቡ ተገቢ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 34778 መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከሳሽ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 343284 ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ እና የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከሳሽ የአሁን አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 376464 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ እና የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ አያስቀርብም ሲል አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ አከራካሪ የሆነው ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር የይዞታ ማረጋገጫ ያወጡ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሮ ባለበትና ይህ ስለመሆኑ ተጠሪ ባልካደበት የስር ፍ/ቤት በምን ሁኔታ የቤቱ ስም ወደ ተጠሪ ሊዞር የቻለበትን ሁኔታ ሳያጣራ መወሰኑ ሥነ ሥረዓት ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ የካቲት 8 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም መጋቢት 1 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረተው ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው ፍ/ቤቶች የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በቀረቡት የሰው ምስክሮችና እና የሰነድ ማስረጃ እናታቸው ወ/ሮ ጡሬ ሚጀና በ288 ካ/ሜ ቦታ ላይ ስትገብር የነበረ መሆኑን ይሄው የመሬት ይዞታ ሲለካ 500 ካ/ሜ መሆኑን በዚሁ መሰረት የከተማ አስተዳደሩ የእናታቸው የውርስ ንብረት የከተማ የመሬት ይዞታ ሲለካ 500 ካ/ሜ በመሆኑ ለወራሾቹ 500 ካ/ሜ መዝግቦላቸው እንዲገብሩበት ያደረገ መሆኑን በኋላም በስምምነት ተከፋፍለው ይዘው እንደሚገኙና ተከሳሽ የእናታቸው ቤት ያረፈበት ቦታ ደርሶት ቤቱን አሳድሶ ኩሽናና ሽንት ቤት ጨምሮ ሰርቶበት በስሙ አስመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ አረጋግጦ ወራሾች የእናታቸውን የውርስ ንብረት ተስማምተው ተከፋፍለው ድርሻቸውን ይዘው የሚገኙ መሆኑ በመረጋገጡ የአሁን አመልካችን ክስ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ተለይቶ የሚታወቅ ወራሽና የውርስ ንብረት፣ ወራሾች በስምምነት ቢካፈሉ እና በስምምነት መከፋፈላቸው ከተረጋገጠ የግድ በፍርድ ቤት የውርስ አጣሪ ተሹሞ በፍ/ቤት ክፍፍሉ ያልተፈጸመ ባለመሆኑ በስምምነት የተደረገው የውርስ ሀብት ክፍፍል ህገ ወጥ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1079 ይህንኑ ደንግጎ ይገኛል፡፡ የአሁን አመልካች፣ በስር ፍ/ቤት ጣልቃ ገብ የነበረው አቶ አበራ ጉታ እና የአሁን ተጠሪ የእናታቸውን የውርስ ንብረት ቤት በስምምነት ተከፋፍለው ድርሻቸውን ይዘው የሚገኙ መሆኑ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች የእናቱን የውርስ ንብረት በስምምነት ተካፍሎ ድርሻውን ይዞ እያለ ለአሁን ተጠሪ የደረሰውን የውርስ ድርሻ እንዲያካፍለው መጠየቁ ካለአግባብ በመሆኑ ክሱ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 376464 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 343284 ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34778 መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የደንዲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 65240 የካቲት 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

3. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም